« ሰዋስወ ብርሃን »

## የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት

# ዓመታዊ መጽሔት

ቍጥር ፪

ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ. ም

አዲስ አበባ

# ቅኔ በኢትዮጵያ

ቅኔን ማን ጀመረው ? የሚለውን ሐረገ ሐሳብ ከማስባችን በፊት ቅኔ በሚለው ሥርወ ግሥ ላይ ከተለያየ አንቀጽም ሆነ ከአንድ አንቀጽ የተለያየ የትርጕም ቅርጽና ይዘት በመስጠት መምህራን ግእዝ ያትታሉ ።

፩/ ቆንቆነ ነቀዘ :— ካለው ግሥ የወጣ ጥሬ ዘር ነው ሲሉ፣ምሥጢሩም ቁንቁን ዕንጨትን ውስጥ ውስጡን እየቦረቦረና እየሸረሸረ እንደ ሚበላው ሁሉ ቅኔም የባለ ቅኔዎችን ልቡና በሐሳብ ሠረገላ እያሽከረከረ በምሥጢር ርቀት አእምሮን ስለሚበዘብዝ በገጸ—ንባብ የማይሰናሰሉትን በምሥጢር ኖራ ይለስኑታል ።

፪/ ሌሎች ደግሞ ቀነየ ገዛ ፤ ካለው ግሥ የወጣ ጥሬ ዘር ነው ይሉና ለማስረጃ ያህል የሚጠቅሱት መጽሐፋዊ ግሥ«ቁሙ እንከ ወኢትሐሩ ዳግመ ውስተ አርዑተ ቅኔ»ገላትያ ፭-፩ በመጥቀስ ቅኔ ከያንዳንዱ ባለ ቅኔ በየጊዜው የሚመነጨው የቅኔ ድርሰት«ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ እንዳለው ነቢዩ ዳዊት ባለቅኔውም አዲስ ምስጋናን በማፍለቅ



ለፈጣሪው መገዛቱን የሚገልጥበት ሕዋሳተ አፍአም ሆነ ሕዋሳተ ውስጥን ለሕሊና አስገዝቶ የምሥጢር ጡብ በመሥራት የሥነ አእምሮን አድማስእየ ካበ የሥነ ፍጥረትን ታሪክ ከማድነቅ ጋር የዓለምን የኑሮ ውጣ ውረድም ሆነ የዕለት ተዕለት ኑሮ ገጠመኝን በቅዱሳት መጻሕፍት መርሕነት የሚ ራቀቅበት መሆኑን ያሳያል ።

፫/ ከዚህ ለየት አልን ያሉት ደግሞ ቀነየ ሙሾ አወጣ ፤ ግጥም ገጠመ ፤ አዜመ ፤ እንጕራጎረ ፤ ዘፈነ ፤ አራቀ ተናገረ ፤ መራ ፤ የሚለውን ግሥ አብነት በማድረግ የሚከተለውን - - ሐተታ ይሰጣሉ ። ይኸውም ሰው ከግል አእምሮው አፍልቆ ለእግዚአብሔር አዲስ ምሥጋና ለማቅረብ ምሳሌ መስሎ ፡ ምሥጢር አመሥጥሮ ፡ ግጥም ገጥሞ የልቡናውን ምኞት፣የአእምሮውን ምጥቀት በማድረት የመጠነ አእምሮውን አድማስ በምሥጢር ከሽኖ ፣ በሐሳብ ርቀት የሚያፈካበትና የሰማዕያኑን ሕሊና በተመስጦ ባሕር የሚያንሳፍፍበት መሆኑን በመመልከት ከዚህ ወጣ ይላሉ ። እንግዲህ ቅኔ የሚለው ጥሬ ዘር ከነዚህ ግሦች የማይዘል መሆኑን ከተረዳን

## ቅኔን ማን ጀመረው ?

ስለ ቅኔ አጀማመር ውጥኑ የቅዱስ ያሬድ መሆኑ የማይታበል ሐቅ ሆኖ ሳለ እንዳንዶቹ ከያሬድ በኋላ መልክ አበጅተው፣ በሕግ ደንግገው፣ ቤት ወስነው ያሁኑን የቅኔ ውበት የሰጡትን ሊቃውንት እንደ ጀማሪ አድርገው ሲቈጥሩ ስማቸውንም እንደሚከተለው ያሳያሉ ።

እነርሱም ፡— ሐዊራ ፣ መንክራ ፣ እስክንድራ ፣ ፖ እስክንድራ ፣ አቢዳራ ይባላሉ ይላሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ ዋድሎች በበኩላቸው ቅኔን የደረሰው ዮሐንስ ገብላዊ ነው ሲሉ ጎንጆች ደግሞ ተዋነይ ነው ይላሉ ። ሌሎችም እንዲሁ ደቀ እስጢፋ ነው የሚሉ አልጠፉም።ይሁን እንጂ ዋድሎች ቅኔን የደረሰው ዮሐንስ ገብላዊ መሆኑን ከማረጋገጣቸውም በላይ የአደራረሱም ዓይነት እንደ ሌሎች ግብር ገብቶ ፣ ምሥጢር አቃንቶ እንደ ወጣ ነው እንጂ በፍልስፍና መንገድ አይደለም ይላሉ ። ስለዚህ የኖበረበትም ቦታ በወሎ ክፍለ ሀገር በምትገኝ አማራ ሳይንት በተባለችው ቦታ ሲሆን፣ያችም ቦታ በዚያን ጊዜ ከተማዋ ደብረ ታቦር ትባል ነበር ። ታዲያ ይህ ዮሐንስ ገብላዊ የተባለው ፊት ብዙዎችን እንዳስተማረ ባይካድም አብነት አድርጎ ያወጣውና በእግሩ የተካው አባ ወልደ ገብርኤል የተባለውን መነኰሴ ነው ። አባ ወልደ ገብርኤል ደግሞ ራሱን አስመስሎ በሞያ የወለደው ሠምረ አብን ነው ። ሠምረ አብ በሚያስተምርበት ጊዜ ጉባኤ አስፍቶ ደቀመዛሙርት አብዝቶ ያስተምር ስለነበር ፣ንጉሡንም አጼ በዕደ ማርያምን ቅኔ እንዳስተማራቸው ይታወቅ ዘንድ ይህን ቅኔ ተቀኙ ይባላል ።



www.ethiopianorthodox.org

«ድኅረ ተሠብረ አጽንዖ ለሰብእናየ ልኍሡት
ኢየሱስ ክርስቶስ በማየ ሐዲስ ጥምቀት»፤
ይህ ጉባኤ ቃና ቅኔ የርሳቸው እንደሆነ ይተረካል ።

ይኸም ሠምረ አብ ለልሂብና ለኤልያስ ማስተማሩ ጽድቅ ሲሆን ፣ አልያም ደግሞ ለተዋነይና ለጽድቅ ወልደ ማርያም አስተማረ ፣ ተዋነይ የጎንጅ መንገድ አባት፣ጽድቅ ወልደ ማርያም የዋድላ መንገድ አባት ሆኑ ።-- የቅኔ መንገድ ልዩነትም ያን ጊዜ ተጀመረ ይባላል ። ምክንያቱም ጊዜው የጦርነት ጊዜ ስለነበርና የግራኝ ወረራም በመካከሉ ብዙ የመገናኘት እጥረት ስለፈጠረ የተዋነይ ደቀ መዛሙርት ቅኔውን ጠፈጥ ፣ አገባቡን ወነስ አድርገው ሲይዙ ጽድቅ ወልደማርያም ግን ጉባኤ ሳይፈታ አብነቱንም ሳያጠፋ ይዞ በመገኘቱ የቅኔን መንገድ ፣ የአገባብን ሥነ ሥርዓት ከነሙሉ ጠባዩ ለመጠበቅ ቻለ ፤ እርሱም በዚያ ሙያ የታወቀ በመሆኑ የርሱን ሙያ የያዙ ሁሉ ጽድቅ እየተባሉ ወንበሩን ይዘው ሲያስተምሩ ኑረዋል ። በዚህም ምክንያት የዋድላ አገባብ ፣ የዋድላ ቅኔ እየተባለ ሲመሰገን ኖሯል ። ስለዚህ በዋድላ መንገድ ሲያስተምሩ የነበሩ ስድስት ጻድቅ እንደነበሩ በታሪክ ይነገራል ። ሆኖም የመጨረሻው ጽድቅ ለጽድቅ ወልደ ማርያም አስተማረ፤ጽድቅ ወ/ማርያም ደግሞ ለማዕበል ወልደ ሕይወት ዘሜጫ አስተማረ፤ ማዕበል ወልደ ሕይወትም ለጌቴ ገሞራ ሚካኤል ደብር አስተማሩ ፤ ከዚህ በኋላ ግን አንዱ መምህር የዋድላውንና የጎንጅውን የዋሸራውንም አጠቃሎ በመያዙ የቅኔን ደራሲነት ባለቤት ለተለያዩ ደራስያን ቢሰጥም የቅኔ ደራሲ ያው ቅዱስ ያሬድ መሆኑ አያጠራጥርም ። ለምሳሌ የድጓው ደራሲ ቅዱስ ያሬድ ሆኖ ሳለ ቤተልሔም ፣ ቆሜ ፣ ተጉለቴ ፣ ዋድሌ ፣ አጫብሬ ፣ ወንጩሬ፣ እየተባለ ይነገርራል ፤ ይህን ልዩነት ሊያመጣ የቻለው የዘመን ብዛትና በመካከሉ የተፈጠረው ጦርነት እንጅ ምልክቱም ሆነ የድጓው ዘር አንድ ስለሆነ ደራሲው ያው ቅዱስ ያሬድ መሆኑን የሚያስተባብል የለም ። እንግዲህ ቅዱስ ያሬድ ቅኔን ከምን አግኝቶ ደረሰው ? የሚለው ሐሳብ አጠያያቂ ሳይሆን አይቀርም፣ የሆነው ሆኖ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰት ከቅኔው ድርሰት የሚቀድም መሆኑ እሙን ነው ።

ስለዚህ የያሬድ የዜማ ድርሰት በአራት ሲከፈል ፡— እነሱም ፩ኛ/ ድጓ ፣ ፪ኛ/ ምዕራፍ ፣ ፫ኛ/ መዋሥዕት ፣ ፬ኛ/ ዝማሬ ናቸው ። እንግዲያውስ ቅኔ የያሬድን መዝሙር መስሎ የሚኼድ በዜማ የሚዘመር በመሆኑና ከቅኔ ድርሰት የዜማ ድርሰት መቅደሙ የማይካድ ስለሆነ ከዜማው ድርሰት ቅኔን ደረሰው ይባላል ። ምንም የያሬድ የዜማ ድርሰት እንደ ቅኔ በየጊዜው ከአዩት ፣ ከሰሙት ባሕር የሚጠለቅ ፣ ከግላዊ ሥነ አእምሮ የሚቀዳ ባይሆንም ከዜማው ድርሰቱ የቅኔ ስሞችን እንደወሰደ በግልጽ ይታያሉ ።



፫/ ምዕራፍ በተባለው ድርሰቱ ምቅናይን ፤

፬/ በዚሁ ምዕራፍ ፣ ሚበዝኁ ፣ ዋዜማ ፣ ይትባረክ ፣ ዘይእዜ ፣ መወድስ ፣ ዞልክሙ የሚለውን ስም ከዜማው ይትበሃል እንደሚገኙ ገሃድነቱ ሥውር አይደለም ።

## ቅኔ በቅዱሳት መጻሕፍት ፤

ቅዱሳት መጻሕፍት የቅኔ መድበሎች እንደሆኑና ጸሐፍቱም የቅኔ ባለቤቶች መሆናቸው የማይዘነጋ ርቀታዊ አተራረክ ነው ። እንዲያውም አንዳንዶቹ ብሉያት ንባብ ፣ ሐዲሳት ፣ ትርጓሜ፣ሊቃውንት ምሥጢር ናቸው ከማለታቸውም በላይ ፣ ወንጌል ሠምና ወርቅ ፣ የጳውሎስ መልክት ሠረዝ ፣ የጴጥሮስ መልእክት ሰንሰለት ይላሉ ። እንግዲያስ በተለይም ወንጌልን ስንመለከት የቅኔን ቤትና ስም አይውረስ እንጅ ሰምና ወርቃዊ ምሥጢሩን ብንገባው፣ምሳሌ ዘርን ፣ ምሳሌ መካልይን ፣ ምሳሌ ደናግልንና ሌሎችንም የምሳሌ አነጋገሮችን ስናይ ፍጹም ሰምና ወርቃዊ ጠባይ ስለሚያሳይ ወንጌል የሠምና ወርቅ መንገድ ቀጥታ በር ናት ብትባል ማጋነን አይሆንም ። ሌሎችም የብሉያት መጻሕፍት የሠምና ወርቅ ጠባይ ንጽጽር ሲኖራቸው በተለይም የዳዊት መዝሙር ፣ ኢዮብ ፣ መሐልይ የቅኔ መጽሐፍ መስለው ይታያሉ ። እንግዲህ ያምሆነ ይህ ቅኔዎች በቅዱሳት መጻሕፍት የነዋሪነት መረጃቸውን ለማብሠር ያህል የሚከተሉትን መጽሐፋዊ ቅኔዎች መመልከቱ ለአስረጅነታቸው አርኪዎች ናቸው ።

፩/ ያዕቆብ ልጆቹን ሰብስቦ ለእያንዳንዳቸው የተለያየ በረከት ሲያድል ይሁዳን«ውርንጭላን በወይን ግንድ ያሠራል ፤ የአህያውንም ግልገል በወይን ሐረግ ፣ ልብሱን በወይን ያጥባል ፤ መጎናጸፊያውን በደም ፤ ዓይኑ ፣ ከወይን ይቀላል፤ጥርሱም ከወተት ይነጣል» ሲል ለጊዜው ሰሙ ልጁን ይሁዳን ሲመለከት፣ ወርቁ ግን ክርስቶስ መሆኑን እንረዳለን ዘፍ.፵፱.፲፩ ።

፪/ « አንሊኬ መኀሌተ ለፍቁርየ ዘአፍርቁ ዐፀደ ወይን ኮነ ለፍቁር በብሔር ጥሉል ውስተ ማእዘንቱ ስለወዳጄና ስለወይን ቦታው ቅኔ እቀኛለሁ ። ዙሪያውን ቆፈረ ፤ ድንጋዮችንም ለቅሞ አወጣ ። ምርጥ የሆነውንም ሐረግ ተከለበት፤በመካከሉም ግንብ ሠራ ።የመጥመቂያ ጉድጓድ ማሰበት ፤ ወይንን ያፈራ ዘንድ ተማመነ ፤ ዳሩ ግን ሆምጣጤ አፈራ»።ይህ ሰሙ ሲሆን፣ወርቁ ግን በዘመነ ብሉይ ያሉትን እሥራኤል ዘሥጋና በዘመነ ሐዲስ ያሉት እስራኤል ዘነፍስ መሆናቸውን ሰምና ወርቃዊ ትርጓሜ ያስረዳል ። ትንቢተ ኢሳይያስ ፭.፩ — ፫ ።

፫/ «ሙሴ እባብን በምድረ በዳ እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጅ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባዋል»ይላል ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ በአርዌ ምድር የተመሰለው ዲያብሎስ ሲሆን ፣ በአርዌ ብርት የተመሰለው ክርስቶስ ነው ። በመሆኑም የ«ከመ» ንጽጽር ቅኔ ይሆናል ።

፬/ «ከጥፋት ውሃ በፊት ኖኅ ወደ መርከቢቱ እስከ ገባበት ቀን ድረስ ሲበሉና ሲጠጡ ፤ ሲያገቡና ሲጋቡ እንደነበሩ የጥፋት ውሃም መጥቶ ሁሉን እንደወሰደ እንዳላወቁ የሰው ልጅ መምጣትም ደግሞ እንዲሁ ይሆናል ። » ይህ የ«ከመ» ንጽጽር ቅኔ ነው ።

፭/ ታዲያ ቅኔ መጽሐፋዊ ነው ከተባለ ፣ ያሬድም በቅዱሳት መጻሕፍት ውጥኑን ከወሰደ ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትም በሌሎች ቋንቋዎች ከተጻፉ ቅኔ በሌሎች ቋንቋዎች የለም ለማለት ያጠራጥራል ።

፪/ በሌላ በኩል ፍጹም ኢትዮጵያዊ ቅኔ መሆኑን የዛሬውን ባለ ፸፰ ቤት ቅኔ በማሻሻልና በማቀናበር መልክ የሰጡትን እንደ ሐዊራ ፣ መንከራ ፣ እስክንድራ ፣ ፖእስክንድራ ፣ አቢዳራ እንደዋድሎች ዮሐንስ ገብላዊ ፣ እንደ ጎንጆች ተዋነይ እንዲሁም ደቀ እስጢፋ የተባሉት ሊቃውንት ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ ፣ ለሊቃውንት መመሪያ የሰጡት አስተዋፅኦ ከያሬድ የቅኔ አመንጭነት ብዙም ያነሰ አይደለም ።

## ቅኔ በቅዱስ ያሬድ ድርሰት ፤

፩/ የትንሣኤ አደራረስ ፡— ሀ— ሚበዝኁ ፣ አመ ሣልስት ዕለት ሞአ ለሞት ገብረ ትንሣኤ በሰንበት ።

ለ/ ብፁዕ ዘይሌቡ ፡— ሠርከ ሰንበት ለጸቢሐ እሑድ ገብረ ትን ትንሣኤ በሰንበት ፣

ሐ/ መውድስ ፡— ፍታሕ ሊተ፤ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን፤በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን ፤ ዐሠሮ ለሠይጣን ፤ አግዓዞ ለአዳም ሰላም እምይዕዜሰ ይኩን ሰላም ።

መ/ ኵልክሙ ፡— ዮም በዛቲ ዕለት ፣ ሰበካ ትንሣኤ አዋልዲሃ ለጽዮን ።

የመጽጉዕ ፡— መወድስ ፣ —ክልሐ ዕውር በውስተ ፍኖት፤ ወገሠጽዎ እለ ይመርኅዎ ከመ ያርምም፤ ወአዕበየ ከሊሀ እንዘ ይበል ተሣሀለኒ እግዚእየ ወልደ ዳዊት ርድዓኒ ።

የደብረ ዘይት ፣ — ፍታሕ ሊተ፤ አመ ይመጽዕ ንጉሥ በግርማ መንግሥት፡ዙኅኔ ድልው ቅድሜሁ፤ነፍስ ትርዕድ፤ወመጻሕፍት ይትከሰታ ለሰምዕ ።

የጸሎተ ሐሙስ ፡ —ክብር ይዕቲ ፤ ወአንተስ ጸላእከ ተግሣጽየ፤ ወአግባእከ ድኅሬከ ቃልየ፤ እመኒ ርኢከ ሠራቂ ትርውጽ ምስ



ሌሁ ፤ ወረሰይከ መክፈልተከ ምስለ ዘማውያን ፤
ዕጣነ ሞገር፡—በ፩ ሃሌታ፡ረፈቀ ምስሌሆሙ በድራር ዘዲበ ኪሩቤል ይነብር ፤ ወሎሙ አርአየ ሥርዓተ ምሥጢር ዘቍርባን ንጉሠ ነገሥት ወእግዚእ ኵሉ ፍጥረት ፤

የዘመን መለወጫ ፤ የቅዱስ ዮሐንስ ዋዜማ ምልጣኖች ፣ ጎየንተ ዋዜማ ቅኔዎች ።

ታኅሣሥ ፳፰ የአማኑኤል ዋዜማ ፣ ምልጣኖች ፣ ጎየንተ ዋዜማ ቅኔዎች፣ እንዲሁም አርባዕቱ ምልጣን ሲኖረው ጉባኤ ቃናው ቅኔ ቀርቶ ምልጣኑ ጎየንተ ጉባኤ ቀና ይሆናል ። የሚሆንባቸውም ሰዓት ሀ/ በመጻጉዕ፤ለ/ በሆሣዕና ፤ ሐ/ በትንሣኤ እንዲሁም አልፎ አልፎ በሌሎች ሰንበታት ጉባኤ ቃናው የሚቀረው አርባዕቱ ባለ ምልጣን በመሆኑ ነው ።

| ተራ ቊ/ | የቅኔ ስሞች | ቤታቸው | የቅኔ ስሞች | ቤታቸው | የቅኔ ስሞች | ቤታቸው |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | ጉባኤ ቃና | ፪ | ፭ አጭር ዋዜማ | ፪ | ፱ ማህልክ | ፫ |
| ፪ | ዘአምላኪየ | ፫ | ፮ ሥላሴ | ፮ | ፲ መወድስ | ፰ |
| ፫ | ሚበዝኁ | ፫ | ፯ ዘይዕዜ | ፭ | ፲፩ ኵልክሙ | ፱ |
| ፬ | ዋዜማ | ፭ | ፰ አጭር ዘይእዜ | ፪ | ፲፪ ሕንጼሃ | ፪ |

| ተራ ቊ/ | የቅኔ ስሞች | ቤታቸው | የቅኔ ስሞች | ቤታቸው |
|---|---|---|---|---|
| ፲፫ | ሐዋርያቲሁ ከበበ | ፪ | ፲፯ ዕዝል ዕጣነ ሞገር | ፲፩ |
| ፲፬ | ግእዝ ክብር ይእቲ | ፬ | | |
| ፲፭ | ዕዝል ክብር ይእቲ | ፬ | | |
| ፲፮ | ግእዝ ዕጣነ ሞገር | ፯ | | |

እንግዲህ ከላይ በሠንጠረዥ እንደተገለጹት በየዓይነታቸው የቅኔ ስሞች ፲፯ ሲሆኑ ፣ በአጠቃላይ ቤታቸው ደግሞ ፸፰ ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

ለዚሁም መረጃ የሚከተለውን ቅኔ ቢመለከቱ የቅኔ ቤቶች ፩፯ መሆናቸውን ያስረዳል ። ማስረጃ ፡ መወድስ ቅኔ ፡ ደቀ እስጢፋ ጻድቅ

ከመ እስክንድር ፡ በመንፈስ ቅዱስ ነበበ ሐሳባተ ነቢይ ቅኔያተ ፤
እምቅኔያ ቲሁ ለያሬድ ዘእንበለ ያትርፍ ምንተ ፤
ወከመ ኢይኅድሩ ውስተ አፍአ ፡ እምቅኔያቲሁ ሐንጸ አብያተ ፤
ሰብዓ ወሰማኒተ፤ ወጠፈረ እሉ አብያት እስከነ ይእዜ ኢተነሥተ ፤
ሐዊራሰ ወመንክራ ዘተጋብኡ ድርገተ ፤
ዘምስለ ብዑል እስክንድር አስተጋብኡ ምሥጢራተ ፤
መንክራተሂ መተሩ ወተመሰሉ መጥባሕተ ፤
ለመጥባሕት እስመ ልማዱ ከፊሎተ ዋሕድ አርባዕተ ።

## የግእዝ ቅኔና የሕዝባዊ ቅኔ ግጥም ልዩነት ፤

፩/ የግእዝ ቅኔን ለማወቅ የሚፈልግ የማንኛውም ቋንቋ ተገልጋይ ሁሉ አፉን ያልፈታበትን የግእዝ ቋንቋ ማጥናት የመጀመሪያ ግዴታው ሲሆን የሕዝባዊ ቅኔ ግጥም ገጣሚ ግን በሚገለገልበት ቋንቋ ይገጥመዋል ።

፪/ የግእዝ ቅኔ በተወሰነ ሁኔታና አካባቢ ሲቀርብ የሕዝባዊውን ቅኔ ግጥም ግን ሁኔታና አካባቢ አይወስነውም ።

፫/ የግእዝ ቅኔ በትምህርት የሚሰጥ ፤ ዜማውንም ያልተማረ የማያዜመው ሲሆን ፤ የሕዝባዊ ቅኔ ግጥም ግን በትምህርት መልክ የማይሰጥ፣ የዜማ አስተማሪ የሌለው ሕዝባዊ ትውፊት ነው ።

፬/ የግእዝ ቅኔ የዜማው ምጣኔም ሆነ የሐረጎች አወቃቀር ብያኔ ሲኖረው፣ የሕዝባዊ ቅኔ ግጥም ግን በትውፊት ጅራትነት የሚጓዝ መሆኑን ያጠይቃል ።

፭/ የግእዝ ቅኔ ሐረግ ፤ ማንደርደሪያ ፤ ቧኄ ፡ ለዓለም ፡ መጽፌያ ፤ ኳኛ የሚባሉ መለያ ሲኖሩት፡የሕዝባዊ ቅኔ ግጥም ግን እነዚህን ሁሉ አያሟላም ።

፮/ የግእዝ ቅኔ በአብዛኛው መልኩ መንፈሳዊ አገልጎሎትን ሲመለከት፡የሕዝባዊ ቅኔ ግጥም ግን በአብዛኛው መልኩ ማኅበራዊ ጉዳዮችን ይዳስሳል ።

፯/ የግእዝ ቅኔ ተሳትፎው በተወሰኑ ሰዎች ብቻ ሲሆን፡ የሕዝባዊ ቅኔ ግጥም ግን ተሳትፎው ሕዝባዊ ነው ።

፰/ የግእዝ ቅኔ የተወሰኑ ባለቤቶች ሲኖሩት ፡ የሕዝባዊ ቅኔ ግጥም ግን ሕዝባዊና ማኅበራዊነትን ያመለክታል ።



## የቅኔ ዓላማ (ጥቅም) ።

፩ኛ/ ለንግግር ፤ ንግግር የቋንቋን ብልጽግናና የማንበብ ዝንባሌ ልምድን የሚጠይቅ በመሆኑ አንድ ባለ ቅኔም የመጻሕፍትን ገላ ቀዶ የምሥጢር መጋዘን ከፍቶ ፡ የሰማዕያኑን አእምሮ አድናቆት የሚያሸምት በት መጀመሪያ ቅኔውን በአካል ምሥጢር ከመላሱ በፊት ስለሚቀረጸው ቅኔ ምሥጢር ጠለቅ ብሎ መቃኘት፡የበዓሉን ታሪክ መጥገብና መጽሐፍ አወቅ መሆን ይጠበቅበታል።ይህን ነገር አንድ ባለ ቅኔ አስተካክሎ ከተገኘ የአእምሮው ማሠሮ የሐሳብ እርሾ ስለማይመትር አድማጩን ሐሳብ ቆርሶ ማጥገብ ይችላል ።

፪ኛ/ የሰዎችን ሐሳብ ለመረዳት ፡ ባለ ቅኔ ምን ጊዜም እያንዳንዱን ኅብረተሰብእ ባህል ፡ ታሪክ ፡ ወግ ማወቅና መገንባት ያለበት በዚሁ ኅብረተሰብእ ውስጥ ያለውን ሁለንታናዊ ሕይወት ሲረዳ በመሆኑና የቅዱሳት መጻሕፍትን ገጸ ንባብ ከነአሥራው ትርጓሜያቸው ዓይነ ሕሊናውን ተክሎ መመርመርና ማሰስ ስለሚፈለግበት፣ ሰዎች ስለሚያቀርቡት ታሪካዊም ሆነ መጽሐፋዊ ጥቅስ እንዲሁም ማኅበራዊ ጉዳዮች ባዕድ ስለማይሆን በቶሎ የመረዳትና በአእምሮ የመቅረጽ ልምድ አለው ።

፫ኛ/ አናቅጸ መጻሕፍትን መተርጐሚያ ፤ ቅኔ አገባብን ፡ ርባታን የአቀፈ ስለሆነና ይህ አገባብና ርባ ቅምር ደግሞ የቅዱሳት መጻሕፍት ሰብል እንደመሆኑ መጠን በየቅዱሳት መጻሕፍቱ ይቃረማል ። ቅኔ በቅዱሳን ፡ በመላእክት በጻድቃን ፡ ዕለት ታሪካቸውንና በዓላቸውን ተመልክቶ የሚመሠጠር በመሆኑ ድርሳናትን ፡ ተአምራትን ፡ ገድላትን አዘውትሮ ማንበብን ስለሚጠይቅ የተጠቀሱትን አዋልድ ፡ መጻሕፍት መዛመድ ያሻል ። ይኸ ከሆነ መጻሕፍቱ በቀላሉ ይነዳሉ ። ቅኔ አጥንቱ ሊጠነክር ሥጋው ሊዳብር የሚችለው ከብሉያት ከሐዲሳት መጻሕፍት ጋር ጉርብትናው ጥብቅ የሆነ እንደሆነ ነው ። ያለበለዚያ «የነልንክድነው ቤት መዝጊያው ጭራሮ ማራው ሰንበሌጥ»እንዲሉ በአናቅጸ መጻሕፍት ያልተሸበበ ቅኔም የምሥጢር ክፍትነት ራቁትነት ይታይበታል።በመሆኑም ነበር በትርጓሜ መጻሕፍት አስተውሎት ያልተላበሰ አእምሮ የጐንደሮችን የሰምገፍ አፍራሽ ቅኔ መንገድ የቅኔውን ገጸ ንባብ ማንበብ እንጅ የቅኔአዊ ርቀትቃታውን ለመፈልቀቅ ዐቅመ አእምሮው የሚአጥረው። እንግዲያስ ቅኔ ሁል ጊዜ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር መገናኘትና ከአስራው ትርጓሜአቸው ጋር መጠንጠን አለበት ።

፬ኛ/ ፍርድን ማስተማርያ (የተቃውሞ ድምፅ መግለጫ) ፤ የቅኔ ዓላማ በነኮርንትን ያላዩ ቅኔን ባለቅኔዎች የወደዱትን ማሞገሻ የጠሉትን ማናናቂያ አድርገው ለማቅረብ እንደሚሞክሩ ቢተባተቡም ቅኔ በግል



www.ethiopianorthodox.org

ሕይወትም ሆነ በማኅበራዊ ሕይወት ፍርድን ማስተማሪያ እንጅ በልቅም
አስተሳሰብና በጠራ አመለካከት ያልተሰለቀ ግርድፍ አመለካከታቸው
የባለ ቅኔዎችን ሒሊና ያቅረዋል እንጂ ባለቅኔዎች የበላይ ባለሥልጣኖች
በሕግ የተጣለውን ፍርድ ከአደፈረሱት በማመልከቻዊ ቅኔአቸው ይግባ
ኙን ለቻሩ አምላክ የሚያቀርቡበት ይልቁንም እንኳን ምድራዊውን የፍ
ርድ ጉድለት ቀርቶ ሰብአዊ ሒሊና መመጣጠን የሚሳነውን ሰማያዊ ፍርድ
በተንጠራራ ኩሸት ብያኔውን ለማከላወስ የአፈረጠመ የምጸት ክንዳቸ
ውን በመላክ የዕውቀት ከምቾችን ከማሰባሰብ ጋር የሚከተሉትን ገስ
ረጃ ማየቱ ይበቃል ።

፩ ኵንኖ ኀጥኣን አምላክ ኢይደልወከ ምንተ ።

አፍቅሩ ጸላዕተክሙ እንዘ ትብል አንተ ።

አምላክ ኃጥአንን መኰነን አይገባህም ፤ አንተ ጠላቶቻችሁን
ውደዱ ብለሀልና ።

፪ ዳዊት ሐሰወ ትንቢተ ዳዊት፤ አምጣነ ዕፄ ተሰምየ ዕፄ እንዘ አልቦቱ።

ገብረ መርዓዊ ይፈጽም ትንቢተ ዳዊት ባሕቱ ።

ውእቱ ዕፄ ወሥጋ ውእቱ ።

ዳዊት በትንቢቱ ዋሸ፤ ምነው ትል ሳይኖርበት እራሱን በትል
መስሎ አልና ፤ ነገር ግን የዳዊትን ትንቢት ገብረ መርዓዊ ይፈ
ጽም፤ ምክንያቱም እሱ ሰውነቱ ቆስሎ ሥጋው ትል ሆኖአል»

፫ ኀድግዎ ወመንንዎ ለዝንቱ ዓለም በብሂሎቱ አምላክ ሐሰወ ወቃለ
ጽድቁ አድከመ ።

ውእቱ አኮኑ አፍቀረ ዓለመ ።

«አምላክ ሰዎችን ዓለምን ናቁት፤ተዋት፤ማለቱ ዋሸቷል፤ ምነው
እሱ ዓለምን ወዶ መጥቷልና ።

እያለ ባለቅኔው የግል ቅኔአዊውን ብያኔ በገፍ ለመጋበዝ ያልዳዳ ።

ስለዚህ ቅኔ የወደዱትን ማጋነኒያ፣የጠሉትን ማኮሰሻ ሳይሆን ፣ ማስተ
ማሪያ ፣ ፍርድ ማስተላለፊያ በመሆኑ እንኳን ምድራዊው ቀርቶ የሰማያዊ
ውን አምላክ ሥራ እንኳ ከላይ በጠቀስኳቸው ምድራዊ የቅኔ መንገዶች
ባለ ቅኔ የማያደላ ቀጥተኛ ሚዛናዊ ፍርድ ሰጥቷል ።

ከመሪጌታ ቀጸላ መንግሥቱ



www.ethiopianorthodox.org